# የፅንፈኛው ተቃዋሚና  የአክራሪው መተቃቀፍ !

ታከለ ዓለሙ

ጽንፈኛነት የከረረና የገረረ እምነትን ማራመድ፣ እኔ የምለው ካልሆነ ብሎ ሰማይ ዝቅ መሬት ከፍ ቢል ከያዘው የፖለቲካ ሆነ የእምነት አቋም ፍንክች አልልም፡ ለውይይት፣ ለንግግርና ለድርድር ቦታ የለኝም የሚል አስተሳሰብ ነው፡፡ ይኸው ፅንፈኛ ወገን የፖለቲካው አክራሪ ክፍል መሆኑ ነው፡፡

በሌላው ወገን ደግሞ የየትኛውም ዓይነት ሀኃይማኖት አክራሪ ወገኖች አሉ፡፡ ከእኛ በቀር እውነተኛና ትክክለኛ የለም፡፡ እኛ ያልንህና የምንልህ የፈጣሪ ትዕዛዝ ስለሆነ ተቀበል፡፡ ከእኛ ውጭ ያለ ሁሉ ታሪኩም፣ ባህሉም፣ እምነቱም መጥፋት አለበት ብለው የሌላውን እምነት ተከታይ ሕይወት ማጥፋትና መግደል እንደ ፅድቅና ገነት እንደመግባት የሚቆጥሩት አሉ፡፡

የፖለቲካው ጽንፈኛም ሆነ የኃይማኖት አክራሪ ኃይሎች በየትኛውም መልኩ ለየትኛውም ሀገርም ሆነ ሕዝብ የሚበጁም የሚጠቅሙም አይደሉም፡፡ በአንዲት ሀገር ብቻ ብዙ የተለያዩ እምነቶች፣ ባህሎች፣ ኃይማኖቶች፣ ቋንቋዎች፣ ብሔር፣ ብሔረሰቦች ሰፊ የአመለካከት ልዩነቶች ያሉና የሚኖሩ በመሆናቸው ሊኖራቸው የሚችለውም ተቻችሎና ተዳማምጠ ተከባብሮ መቀጠል መቻል ነው፡፡

የፖለቲካው ፅንፈኛም ሆነ የኃይማኖቱ አክራሪ ይህን ሰፊ ልዩነቶች የመቀበልና የማስተናገድ አቋም ስለማይቀበል አደጋው መገመት ከሚቻለውም በላይ የከፋ ነው፡፡ ፅንፈኛነትም ሆነ አክሪሪነት ለሀገርም ሆነ ለኅብረተሰብ ከአደጋም በላይ ታላቅ ውድመትን፣ ጥፋትንና እልቂትን የሚያስከትል የአደጋዎች ሁሉ አደጋ ነው፡፡

በአብዛኛው ከኢትዮጵያ ውጭ በምዕራቡ ዓለም የሚኖረውና የሚሰራው ኢትዮጵያዊ ኑሮውን ለማሸነፍ በተለያዬ መስክ ተሰማርቶ ይሰራል፡፡ በተለይም ለሚሊዮን ትንሽ የሚቀረው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚኖረውና የሚገኘውም በአሜሪካን የተለያዩ ስቴቶች ነው፡፡ ከንጉሡ ጊዜ ጀምሮ በኋላም በደርግ ዘመንና ከደርግ ውድቀትም በኋላ የየሥርዓቱ ከፍተኛ ሹሞች በተለያየ ደረጃ ያሉ ከፍተኛ ኃላፊዎች በስደትም የዲቪ ሎተሪ ደርሷቸው የሄዱትም ሁሉም እንደቆይታቸው ዜግነት አግኝተው ይኖራሉ፤ ይሰራሉ፡፡

በእውቀት የበለፀጉና ትልቅ ደረጃ የደረሱ በዮኒቨርስቲዎችና በየምርምር ተቋማት በመንግሥትና በግል የሚሰሩ ኢትዮጵያውን ቁጥር ከፍ ያለ ነው፡፡ እዚያ ሁነው ወደ ኢትዮጵያ ገንዘብ በመላክ ብዙ ቤተሰብ የሚረዱና የሚያግዙ አሉ፡፡ ከፍተኛ አቅም ገንብተውና ሀብትም ይዘው በኢንቨስትመንት የተሰማሩ፣ ለሀገራቸውም ድርሻቸውን እየተወጡ የሚገኙም አሉ፡፡ ከዲያስፖራው 90 በመቶ የሚሆነው ሕይወቱን ለመለወጥ ሠርቶ በመኖር ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ እነዚህ የሀገር

መኩሪያና የሀገር ሀብቶች ናቸው፡፡ ልምዳቸው፣ እውቀታቸውና ገንዘባቸው ለኢትዮጵያ በእጅጉ ይጠቅማል፡፡ በሀገራቸው ጉዳይም ድርቅ ሲከሰት፡ ረሀብ ሲመጣ፡ በጦርነት ሆነ በልማት ወቅት፡ በሕዳሴው ድልድይ ግንባታና በመሳሰሉት የአቅማቸውን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ አላሉም፡፡

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ በደርግና በኢሕአዴግ ዘመን በኢትዮጵያ በተለያየ መንግሥታዊ ተቃዋሚነት ታሰረው የወጡና በስደት አሜሪካን ሂዴው የሚኖሩ ጥቂት ክፍሎች አሉ፡፡

በፖለቲካ ተቃዋሚነት ተሰማርተው ሕይወታቸውን የሚገፉ፣ አሜሪካ በሰፈነው ዴሞክራሲ፣ ከተለያየ የዓለም ክፍል ሂዶ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በቋንቋና በባሕል ወዘተ. የተለያዩ ሕዝብ ቢሆኑም በጋራ በመሰረቱትና ባቆሙት አሜሪካ ሁሉም ለጋራ ሀገሩ በጋራ የሚሰራበት ተከባብሮና ተቻችሎ የሚኖርባት፡ መብቶችም ድምፅም በእኩልነት የሚከበሩበት ሀገር ነው የመሰረቱት፡፡ የግለሰብም ሆነ የቡድን አመለካከቶች በነፃነት የሚከበሩበት፣ ከሕግ ውጭ አንዲት ሴ.ሜ መራመድ የማይቻልበት ሀገር ነች አሜሪካ፡፡

አሜሪካን መቀመጫቸውን ያደረጉት የተለያዩ ስም ያላቸው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የቀኝ መስመርም ያራምዱ የግራ ወይንም የኒዮ - ሊበራል አቋም ከአንተ እኔ እሻላለሁ በሚለው የእርስ በእርስ መነቃቀፍ መወነጃጀል ረዥሙን የእድሜ ዘመናቸውን ገፉት፡፡ አንዱ በአንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ ነው ነገሩ፡፡

በአንድ ወቅት በቃ የኢትዮጵያን ችግር ለመፍታት ልዩነቶቻችን እንዳሉ ሆነው ለአንድነት በሕብረት ጥላ ስር መሆን አለብን ብለው ብዙ መክረው ይሰባሰባሉ፡፡ ሕብረት ይፈጥራሉ፡ ጥምረት ይፈጥራሉ፡ ቅንጅት ይፈጥራሉ፡፡ ፎረም ይፈጥራሉ፡ መድረክ ይፈጥራሉ፡፡ አንድና ሁለት ወር ጊዜ ሳይሞላቸው እርስ በእርስ መናቆር መናጨት ጀምረው ሕብረቱ ይፈርሳል፡፡ አንዱ ሌላውን በመንግሥት ሰላይነት ወይንም በአድርባይነት ይከሳል፡ ይወነጅላል፡፡ እድሜ ለአሜሪካ ሁሉም ራዲዮ ጣቢያ አለው፡፡ በዛ ራዲዮ ጣቢያ አንዱ በሌላው ላይ ይዘምታል፡፡ የስም ማጥፋት ፕሮፓጋንዳ ያካሂዳል፡፡ አንደኛው ለኢትዮጵያ ከእኔ የተሻለ የሚያስብ ወይንም የሚሰራ የለም ይላል፡፡ የፈጠሩት መሠረቱ ያልተገነባ ሕብረት ቅንጅት መድረክ ይፈርሳል፡፡ ግብግቡ እዚያው ይቀጥላል፡፡ ሁሉም በየፊናው አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ በየስቴቱ መዋጮ ይጠይቃል፡፡ እውነት ለኢትዮጵያ የተሻለ ሊሰሩ ይችላሉ ብሎ ለሀገሩና ለወገኑ ካለው ፅኑ ፍቅር በመነሳት የሚያዋጣው መዋጮ በአብዛኛው ተበልቶ በግለሰቦች እጅ ይጠፋል፡፡

ፅንፈኛው ዲያስፓራ ከፖለቲካ አክራሪነቱም ባለፈ እጅግ በከፋና ሊገለፅ በማይቻል ጥላቻ የተዋጠ በመሆኑ፤ መቻቻልና በልዩነት መከባበር፣ ለጋራ ሀገር ከእነሱ ርቆ ያለውም የተለያዩ ብሔር፣

ብሔረሰብ ባለመብት ባለጉዳይ መሆኑንም ይዘነጉታል፡፡ በጎሳና በዘር ፓለቲካ ላይ ተመሰርተው ልቅና መረን የሆነ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ያካሂዳሉ፡፡ ከየትኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ብሔር ብሔረሰቦች የተገኘን ሰው ጥፋት ካለው ግለሰቡን መንቀፍ መተቸት መውቀስ ይቻላል፡፡ ጎሳና ዘር ላይ ስድብና ጥላቻ ውግዘት ማካሄድ ግን ኢትዮጵያን በመሰለ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ባሉበት ሀገር ለአብሮነትና ተከባብሮ ጠንካራ ሀገር ለመገንባት የሚደረግውን ጥረትና ትግል ይንደዋል፡፡ ያፈርሰዋል፡፡ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ፓለቲካ ቢገባውም ባይገባውም ብሔረሰቡ ስለተነካ ብቻ በሌላ ጎራ ለትግል ይሰለፋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ያልሰከነ ብስለት የጎደለው የኢትዮጵያን ታሪክና ኢትዮጵያዊነትን በቅርቡ ካለመረዳት የሚመጣ ፅንፈኛ ተቃዋሚ ፓለቲከኞች የሚፈጥሩት ስር የሰደደ ችግር ለሀገሪቱና ለሕዝቦች አንድነት አደጋን ያስከትላል፡፡

የተሻለች ሀገር እንገነባለን የሚለው ፅንፈኛና አክራሪ የዲያስፓራው ተቃዋሚ ያልተገመተ አደጋ በሀገሪቱ ላይ እንዳያመጣ መጠንቀቅና ማስተዋል የሁሉም አስተዋይ ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡ ሁሉም ዜጋ በሀገር ውስጥና በውጭ ያለውም ጭምር በተለያ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የተለያ አመለካከት አለው፡፡ ይኖረዋልም፡፡ ይህም መሠረታዊ ተፈጥሮአዊ መብቱ ነው፡፡

ሁሉም አንድ ዓይነት አስተሳሰብና አመለካከት ይኑረው ወይንም ይኖረዋል ብሎ ለማሰብ አይቻልም፡፡ ቢያንስ ግን መሠረታዊ በሆነው የሀገር ሕልውናና ደህንነት የሁሉም የጋራ ቤት በሆነችው ኢትዮጵያ ሠላም ላይ ብዙ ልዩነት ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ሀገር ውስጥም በውጭም ያለው ዜጋ እትብቱ የተቀበረባት በቀዬዋ ባርቆ ያደገባት የተማረባት አያት ቅድመ አያቶች በመስዋዕትነት ጠብቀው ታሪክ ሰርተው አስከብረው ያቆየዋትና ለተረኛው ትውልድ ያስረከቧት እያንዳንዱ ከታሪኳ፣ ከባህሏና ከእምነቷ የሚጋራና በደምና አጥንት የተሳሰረ ታሪክ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

የጋራ ቤት የጋራ ታሪክ ያለባት ዞሮ መግቢያና መሰብሰቢያ በመሆኑ ነው፡፡ ከጥላቻ ፓለቲካም ወጥቶ ሰከኖ ማሰብ በመከባበር፣ በመደማመጥና በመቻቻል መንፈስ ልዩነትን በወጉና በአግባቡ ይዞ ለጋራ ሀገር መቆም ከቂም በቀል አስተሳሰብ መውጣት የሚበጀው የሁላችንም የጋራ እናት ለሆነችው ኢትዮጵያና ለሕዝቧ ለእድገትና ለልማቷ ነው፡፡

ከዚህ ውጭ ያለው መንገድ ከጥፋትና ከውድመት እንደገናም የሀገሪቷን እድገት ወደ ኋላ ከመጎተት ውጪ አንድም ምንም ለውጥ አያመጣም፡፡ የፅንፈኛ ፓለቲከኞቹና የአክራሪዎች መታቃቀፍ በሀገር አሜሪካ ሆነው የሚንቀሳቀሱት ኢትዮጵያውያን የፓለቲካ ተቃዋሚ ድርጅቶች በአብዛኛውም ፅንፈኛ የፓለቲካ አቋም አራማጆች ናቸው፡፡

በሠላማዊና በምርጫ ውድድር የማያምኑ ኢሕአዴግን ከሚቃወም ክፍል ከሠይጣንም ጋር ቢሆን ተባብረን በሕዝብ አመፅና በጠመንጃ ኃይል ከሥልጣን አውርደን እኛ ወደ ሥልጣን መምጣት አለብን ወይንም እንመጣለን ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡

በቅርቡ ዓመታት የተመሠረተው ግንቦት 7 የፓለቲካ ድርጅት ኢሕአዴግን በምርጫ ሳይሆን በጠመንጃ ኃይል ማወረድ እችላለሁ ብሎ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ በእርዳታ ባሰባሰበው ገንዘብ ኢሣት›› የተባለውን የሣተላይት ቴሌቪዥን ጣቢያ ከፍቶ የሀሰት የቅስቀሳ ፕሮፓጋንዳዎችን እየረጨ ይገኛል፡፡ ስለ ኢሣት ውሸትና ቅጥፈት በተጨባጭ ብዙ ማለት ይቻላል፡፡

በዶክተር ብርሀኑ ነጋ የሚመራው ግንቦት 7 ከሻዕቢያ ጋር ግንኙነት ፈጥሮ አሥመራ ድረስ በመመላለስ እየሰራ ይገኛል፡፡ ከግብፅ አዲሱ መሪዎች በተለይም ከውሀ ሚኒስትሩ ጋር በፈጠሩት ግንኙነት የግብፅ ውሀ ሚኒስትር የአባይን ውሀ በተመለከተ ከአቶ መለስ ዜናዊ በኋላ ከሚመጣው መንግሥት ጋር በሠላም እንሰራለን›› ሲሉ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

በዘመናት ታሪካችን ያልተቻለውንና ያልተሞከረውን የሕዳሴውን ግድብ (አባይ ወንዝ) እንዲገደብ ያደረገና ለኢትዮጵያ እድገትና ልማት የሰራና የደከመን፤ ለቀጣዩ ትውልድ የታሪክ አሻራን ያስቀመጠና ለብሔራዊ ጥቅማችን የታገለን መሪ ግብጾች በሞቱ ቢደሰቱ፡ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፈው ሰጥተው አብረው ለመስራት ቢመኙ ምን ይገርማል?

በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ በሕዳሴው ግድብ የተያያዘችውን ግንባታ ለማቋረጥ ወይንም አቅሙን ለመቀነስ ሥልጣን ከያዝን እኛ እናደርገዋለን ብለው እነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ከግብጾች ጋር መክረዋል;፡፡ ተስማምተዋል፡፡ ይህን መሠረት አድርገው ነው የግብፁ የውሀ ሚኒስትር ደፍረው መግለጫ የሰጡት፡፡

እነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ገና ሥልጣን ላይ ሳይወጡ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለመሸጥ ከግብፅ መሪዎች ጋር ከተደራደሩ ሥልጣን ቢይዙ ደግሞ ሀገሪቱን ቸብችበው ሸጠው ይጨርሱአታል ማለት ነው፡፡ ደግነቱ በዚህ አጋጣሚ የእነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ውስጣዊ ማንነት በገሀድ ተጋልጦ በመውጣቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቁሙ ሊሸጡት የሚያሰማሙትን ከሀዲዎች መቼም እንደማይቀበላቸው በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

በግብፅ በአሁኑ ወቅት ሥልጣን የያዘውና በምዕራባውያን የሚነቀፈው በሲ.አይ.ኤ ጥቁር መዝገብ ውስጥ ይገኝ የነበረው የቀድሞውን የግብፅ ፕሬዚዳንት በጦር ሠራዊት አባሉ አማካይነት ያስገደለው የሙስሊም ብራዘር ሁድ ፓርቲ ነው፡፡ ሙስሊም ብራዘር ሁድ አክራሪ እሥልምናን አራማጅ ሲሆን በተለያ የዐረብ ሀገራት ውስጥም ተቋቁሞ ሰፊ አባላት አፍርቷል፡፡ ከዐረቡ ዓለም ሁከትና ነውጥ ጀርባም ሙስሊም ብራዘር ሁድ ፓርቲ ነበር፡፡ በሊቢያ፣ በየመን፣ በቱኒዚየ ወ.ዘ.ተ፡፡ በኢትዮጵያም ይኼን ፓርቲ በገሀድ ባያቋቁሙም ሀሳቡ ስር ሰዶ ኢትዮጵያውን አክራሪ ሙስሊሞችን ለማደራጀትና ለፓለቲካ ሥልጣን ለማብቃት እንቅስቃሴዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ወደ ኢትዮጵያ የተነባጠረውና ወደ ሀገር ውስጥ የገባው የአክራሪ ሙስሊም እምነት ከሣዑዲ ዐረቢያ ነው፡፡ የሣዑዲ ቢሊዬነር ዋሀቢዎች የነዳጅ ሀብታም ቢሆኑም ሕዝባቸውን የሚቀልቡበት ለምና ለምለም መሬት የላቸውም፡፡ ይኼ ችግር እጅግ ያሳስባቸዋል፡፡ ስለዚህም ኢንቨስተሮቻቸው በሌላው ሀገር መሬት በሊዝ እየያዙ ይሰራሉ፡፡ ኢትዮጵያም ገብተዋል፡፡

ከኢንቨስትመንቱ ውጪ ሌላው ትልቁ የሣዑዲ አክራሪ ቀሣውስትና ንጉሣዊ ቤተሰቦች የዋሀቢ እምነት ትስስር አላቸው፡፡ በለምለሚቱ ኢትዮጵያ ላይ ዓይናቸው ካረፈ ቆይቷል፡፡ ስለዚህም የዋሀቢ አክራሪ እሥልምናን እምነት በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ውስጥ ቀስ በቀስ ማስረፅና ማስፋፋት በገንዘብ መደገፍ፣ ሙስሊሞች በብዛት እንዲወልዱ ማድረግ ችግር እንዳይኖርባቸው ኢትዮጵያ ባሉ መንግሥታዊ ባልሆኑ እስላማዊ ድርጅቶች አማካኝነት ድሆችን መርዳት በሚል ሽፋን ከፍተኛ የገንዘብ ፈሰስ በማድረግ ማሳደግ፡ ቁርዓን በዋሀቢዊች መድረሳ ትምህርት ቤት ማስተማር፡ የጥንቱን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሱፌ እምነትን፡ መስጊዶችን ፅሁፎችን ማጥፋት፡ ታሪክ አዋቂ የሱፌ ሼሆችንና ኡለማዎችን የታሪክ አሻራ እንዳይኖረው መግደል፡ ሕዝቡ በወልይነታቸው የሚያምንባቸውን የሞቱ ሼሆች መቃብር ቆፍሮ አውጥቶ ማቃጠል፡ ወዘተ ውስጥ ውስጡን ሲሰሩበት ኖረዋል፡፡ በሂደትም ተከታይ አብዝቶ በኢትዮጵያ ፓለቲካ ሥልጣን በመያዝ በሸረዓ የሚተዳደር መንግስት መፍጠር ቆርጠው ከተነሱበት ዓላማቸው ነው፡፡

በሣዑዲ ዐረቢያ በድብቅ የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ሳያውቀው ሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክፉኛ በሚጎዳ መልኩ በኤምባሲዎች፣ በነጋዴዎችና በተለያየ ዘዴ ሲገባ የኖረውና ሲሰራበት የቆየው ገንዘብ ዋና ዓላማው ይኸው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ከፍተኛ እሥልምና ጉባኤን በባለቤትነትና በብቸኝነት በመያዝ የዋሀቢ አክሪሪ እሥልምና እምነት ማስራጫና ማከፋፋያ ማዕከል ለማድረግ ያደረጉትም የሽፋን ትግል በተጨባጭ ተጋልጧል፡፡ ሠላማዊውን ሕዝበ ሙስሊም በማያውቀውና ዋሀቢዎች ብቻ በሚያውቁት ምስጢራዊ የፓለቲካና ጅሀድ ዓላማቸው ቀስቅሰው ለማሰለፍ ከሣዑዲ ዐረቢያ ተቀርጾ የመጣ ኢትዮጵያዊው የዋሀቢ መሪ የሚያሳተላልፈው የተነሱ መልዕክት መሳሪያ በታጠቁ የጅሀድ ተዋጊዎች ወታደራዊ እንቅስቃሴ የታጀበ ሲዲ ፊልም በአዲስ አበባ በክልሎች ተሰራጭቷል፡፡ የተበተነው ወረቀትም የዚሁ አካል ነው፡፡

በመስጊዱ አመራር በአወልያ ትምህርት ቤት ጉዳይ የተነሳው በሙስሊሙ ስም የቀረበ በዋሀቢ አክራዎች የተቀነባበረው አስተዳደር መስል ጥያቄ በውስጡ የያዘው እውነተኛ ጉዳይ ይኼ አልነበረም፡፡ አስተዳደራዊ ችግር አልተፈታም መንግሥት በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ገብቷል፣ አስሮናል፣ ገሎናል፣ የሚለው ጩኸት ከጀርባው የተቀነባበረ የዶክተር ብርሀኑ ነጋ ግንቦት 7 ድርጅትና የሌሎችም ከሙስሊሙ ተነስቶ ክርስቲያኑን ጨምሮ ሰፊ አመፅ እንዲቀጣጠል ተጠንስሶ ሲሰራበት የቆየና አሰቀድሞ መንግሥት ስለደረሰበት ሁኔታው እንዲገታ ተደርጓል፡፡

“የሙስሊሞቹ ጥያቄ ሕጋዊ ነው፡፡ መንግሥትም አስሯቸዋል፣ ገድሏቸዋል፣ አዲስ አበባ ውጥረት ላይ ነች፡፡ ሁኔታው አደገኛና ወደ ከፋ ሁኔታ ሊሸጋገር ይችላል፡” እያሉ እነ ኢሣት እና ሌሎችም የተቃዋሚ ድረ ገፆች (ዌብ ሣይቶች) በሰፊው በአማርኛና በእንግሊዘኛ ሲያሰራጪት የነበረው ሰፊ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ እነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ የነደፉት ስትራቴጂ የዐረቡ ዓለም ሙስሊሞች ተበደሉ ብሎ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ እንዲያኮርፍ፣ ሕዝቡም እንዲቀየም ሲሆን በሌላ ጎኑ ከዐረቡ ዓለም ሰፊ የገንዘብ ድጋፍ እንዲፈስላቸው፣ ቢሮ ለመክፈት እንዲችሉም በማቀድ የተሰራ ሥራ ነው፡፡ ይህ ነው የዶክተር ብርሀኑና ሌሎች እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል! ዓላማቸው፡፡

የዶክተር ብርሀኑ ግንቦት 7 ድርጅትና ሚዲያው አሁን በግብፅ ሥልጣን ከያዘው የሙስሊም ብራዘር ሁድ ፓርቲ መሪዎች ጋር የፈጠሩትም ወዳጅነትና ስምምነት የግብፁ ባለሥልጣን በግልፅ እንዳስቀመጡት ከአቶ መለስ በኋላ በኢትዮጵያ ወደ ሥልጣን ከሚመጣው አዲስ አመራር ጋር በአባይ ወሀ ጉዳይ ችግር አይኖርብንም›› ሲሉ መናገራቸው ተጨባጭ ማስረጃ ነው፡፡ ግብጾች ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቷ በሆነው የአባይን ውሀ ለራሷ እንዳትጠቀምና እንዳትሰራበት፣ አቅም እንዳታገኝ፣ ኢኮኖሚዋም ገዝፎ እንዳያድግ በተለያዩ ዘመን ከጀርባ ሆነው ኢትዮጵያን ለሚወጉ ኃይሎች ሲያግዙ ኖረዋል፡፡ ከሶማሊያና ከሻዕቢያም ጀርባ ሆነው በመሣሪያ ትጥቅና በሥልጠና በማገዝ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያን ወግተዋል፡፡ በአንድ ወቅት ኢትዮጵያ የአባይን ውሀ ብትገድብ ጦርነት እናነሳለን ብለው ዝተውም ነበር፡፡

ኢትዮጵያ የአባይን ወንዝ ገድባ ለመጠቀም በተለያ ጊዜ ለዓለም አቀፍ ተቋማት ያቀረበቻቸው ገንዘብ ጥያቄዎች ወድቅ የተደረጉት ከጀርባ በግብፅ ግፊት ከፊት ለፊት ደግሞ ኃያላን መንግሥታት በሚያደርጉት ተፅእኖ እንደነበር ይታወቃል፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ ከውጭ እርዳታ ምንም ሳትጠብቅ የአባይን ግድብ (የሕዳሴው ግድብ) ለመገደብ ቆርጣ ስትነሳና ሥራ ስትጀምር ግብፆች ምንም ማድረግ ባይችሉም ሂደቱን ለማስናከል ጥረት እንዲሚያደርጉ ይታወቃል፡፡ እነ ዶክተር ብርሀኑ ከዚህ በላይ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ባህል፣ እምነትና ትውፊት ከመሸጥ በላይ ምን አለ? የፓለቲካ ልዩነትንና ብሔራዊ ጥቅምንና ደህንነትን እንኳ መለየት አልቻሉም እነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋና ፅንፈኛው የፓለቲካ ተቃዋሚ፡፡ የቆሙበትም ምስጢር ይኸው ነው፡፡

የጠላቴ ጠላት ወደጄ ነው በሚልና ኢሕአዴግን ለመጣል ከሰይጣንም ጋር ተባብረን እንቆማለን ብሎ በተናገረው መሠረት ኢትዮጵያንና ታሪኳን ለማጥፋት ብሎም የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ "ካዋራጃ" የተባለ ታጣቂ ቡድንም አሰማርቶ ቤተ ክርስቲያንና መስጊድ ሊያቃጥል ከነበረው ክርስቲያን እናቶችና አባቶችን፣ ሙስሊም አዛውንቶችን፣ ሼሆችን በጥይትና በሰይፍ ሲቀላ ከነበረው የዋሀቢ እሥላማዊ አክራሪ ጎን ተሰልፈው ድጋፋቸውን በመስጠት ይከራከራሉ፡፡

የእነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ግንቦት 7 ድርጅት የእነሱ ልሣን የሆነው ኢሣት የሣተላይት ቲቪና ራዲዮ ጣቢያ ሽንጣቸውን ገትረው ለአክራሪዎች ሲከራከሩና ሲሟገቱ በብዙ ሚሊዮን በሚቆጠረው የተለያ እምነት ተከታይ በሆነው ኢትዮጵያዊ (ኦርቶዶክስ፣ ሙስሊም፣ ካቶሊክ፣ አይሁድ፣ ፕሮቴስታንት፣ ዋቄ  ፈታ ባህላዊ እምነትና ኃይማኖት) ላይ ገሀድ ጦርነት ማወጃቸውን፣ የሕዝብ እምነትና መሠረት ማጣቻቸውን፣ የግድ ሊያውቁት ይገባል፡፡

የእነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ስትራቴጂ ለአክራሪ የሰጡት ሙሉ ድጋፍ ታላቅ የፖለቲካ ውርደትና ክስረት እንዲከናነቡ አድርጓቸዋል፡፡ ኢሕአዴግን በአመለካከት በፖለቲካና በፖለቲካ መስመር ልዩነታቸው ሊታገሉት ይችላሉ፡፡ ይኼ መብታቸው ነው፡፡ ኢሕአዴግን ጠላሁ ከሚል ጭፍን ጥላቻ በመነሳት የኢትዮጵያን ስም ወደ ፊት መክረንበት እንቀይራለን ብሎ ስሟንም ታሪኳንም ጭራሹኑ ለማጥፋት ወስኖና ኢትዮጵያውያንን መልምሎ በዋሀቢ እሥላማዊ አምነት አጥምቆ ካዘመተ ፀረ - ኢትዮጵያ ኃይል ጋር የእነ ዶክተር ብርሀኑ ነጋና ሌሎች ተቃዋሚዎች አብሮ መሰለፍ ግን ከፀረ - ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር ለመቆማቸው ከዚህ በላይ ማረጋገጫ የለም፡፡